## ምድብ አምስት (ከ10ኛ — 12ኛ) ክፍል

## 26 ኛ ሳምንት

## ሆሣዕና በአርያም

### ዓላማ

- ቤተክርስቲያናችን የምታከብረው ሆሣዕና እና ሕማማት ላይ ተመርኩዘን፤በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ መኖርን መማር።

### የሚጠና ጥቅስ

- *« ሆሣዕና በጌታ ስም የሚመጣ የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው።»* ዮሐ.12÷13

### መግቢያ

- ከኒቆዲሞስ ረቡዕ (ያለፈው ረቡዕ) እስከ እሁድ ያሉት ቀናት በቤተክርስቲያን የሆሣዕና መዝሙር እና ምንባብ የሚሠማባቸው፤ትምህርትም የሚሠጥባቸው ቀናት ናቸው።
- ሆሣዕና መድኃኒት ማለት ነው።
- ጌታችን ዓለምን ለማዳን ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ÷ ሕጻናትና አዋቂዎች የዘመሩት ስለሆነ በቤተክስቲያን በየዓመቱ ይታሠባል።
- አራቱ ወንጌላውያንም ይሄንኑ ታሪክ ጽፈውልናል/ማቴ.21÷1-16ማር.11÷1-10ሉቃ 19÷20-40 ዮሐ.12÷12-19/
- ይህን የሆሣዕና ቀን‹‹*ከፋሲካ በፊት ስድስተኛው ቀን*›ዮሐ.12÷1 ብሎ ዮሐንስገልጦታል። የቤተክርስቲያናችን አባቶችም ይሄንኑ የወንጌል ቃል በሚገባ አጥንተው በዓሉን በሥርዓተ ቤተክርስቲያን ሠርተውልናል።
- ጌታችን አልኣዛርን ከሙታን ካስነሣ በኋላ የአይሁድ አለቆች በከፍተኛ ቅናት ሊገድሉት ፈልገዋል።
- በዚህ ጉዳይ እየተማከሩ ነው ረቡዕ አልዓዛርን አስነስቶት እሁድ እየሩሳሌም የገባው። ዮሐ.11÷45-57
- ሕዝቡና ሕጻናት ግን የዓለሙን ንጉሥና መድኃኒት በክብር ተቀብለውታል።በዛሬው ትምህርታችንም ይሄንኑ ታሪክና ስለ ሰሞኑ በዓልና መታሠቢያ እንዲሁም እግዚአብሔር ስለእኛ ያለውንና ፍቅር እኛም ለርሱ ሊኖረን ስለሚገባ ፍቅር እንማራለን።

### ትምህርቱ

- ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአይሁድ በዓለ ፋሲካ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ሲገባ በኢየሩሳሌም በዓል ለማክበር የተሰበሰበው ሕዝብ አልዓዛርን ከሞት ማስነሳቱን ስለሰሙ ብዙ ሕዝብ ሊቀበለው ወጣ።

### ሆሣዕና

- ወደ ኢየሩሳም ከመውጣቱ በፊትም ሁለት ደቀመዛሙርቱን *« በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ÷ በዚያን ጊዜም የታሰረችን አህያ ውርንጫም ከእርስዋ ጋር ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁ አምጡልኝ። ማንም እንዳች ቢላችሁ፦ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ፤ወዲውም ይሰዳቸዋል።»* ማቴ. 21÷2-3
- ደቀመዛሙርቱ እንደታዘዙት ሄደው አገኙ።ፈትተው ሲመጡም የአህዮቹ ጌታ ጠየቃቸው ጌታ መፈለጉን ሲነግሩትም ሰደዳቸው
- ጌታችን በውርንጫይቱ (ወጣትዋ አህያ ላይ) ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ።ሕዝቡ ልብሳቸውን የዘንባባ ዝንጣፊና የሌሎች ዛፎች ጫፍ እየቆረጡ መንገድ ላይ በማንጠፍ ተቀበሉት።
- ሕጻናትም *« ሆሣዕና በአርያም በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው። »* እያሉ ዘመሩ።
- ደቀ መዛሙርቱ እንዲሆኑ ጌታችንና መድኃኒታችን የመረጣቸው ቅዱሳን ሐዋርያት የሆነውን በመጀመሪያ አላስተዋሉም ነበር።በኋላ ግን ነቢያት ቀድመው ተንብየው እንደነበርና ያም መፈጸሙን አስተዋሉ።

- ነቢይና መዝሙረኛው ዳዊት *«ከሕፃናትና ከሚጠቡ አፍ ምሥጋናን ለራስን አዘጋጅህ»* መዝ. 8÷2 ሲል ቀድሞ ተንብዩ ነበር።
- በነቢዩ ዘካርያስም « ***ለጽዮን ልጅ፦ እነሆ ÷ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል በሉአት*** »ትን. ዘካር. 9÷9 ተብሎ የተነገረው ተፈጸመ።

<u>ሕማማት</u>

- ጌታችን ስለእኛ መከራ ተቀብሎ እንዳዳነን የምናስብበት ሰሞን ነው። ***"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና።"*** ዮሐ. 3÷16 ተብሎ እንደተጻፈ።
- አምላካችን ለእኛ ያለውን ፍጹም ፍቅር የገለጠበትና ያዳነበት ሰሞን ስለሆነ ይሄንኑ ፍቅር በማሰብ በጾም፣በጸሎት በስግደት እናስበዋለን።
- ቤተክርስቲያናችንም ቀይና ጥቁር ምንጣፎችና መጋረጃ በማድረግ ፍቅሩንና ሕማማቱን በኃዘን ትገልጣለች።

<u>ለእኛ የሆነ የእግዚአብሄር ፍቅር "ሀ"</u>

- ለእኛ የሆነ የእግዚአብሔር ፍቅር ምንኛ ታላቅ ነው! እግዚአብሔር ፍቅር ነው ማለት ብቻ ለዚህ በቂ ነው።ስለ እኛ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል። ***"እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን።"*** 1ኛ ዮሐ 4፡19።የፈጠረን እኛ ሳንወደው አስቀድሞ እርሱ ስለወደደን ነው።
- ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣ የፈጠረን በራሱ መልክና ምሳሌ ነው፤
- እርሱ እኛን የፈጠረን ሁሉንም ነገር ካዘጋጀልን በኂላ ነው።ሰማይ ጣሪያ እንዲሆነን ከፍ ሲደርግልን ምድርንም በላይዋ ላይ እንድንራመድ ለእኛ አስተካክሎልናል።እርሱ ብርሃንን፣ውኃን፣አትክልቶችንና ገነትን አዘጋጅቶልናል።
- ከዚህ በኂላ እኛን ፈጠረን ።
- በኃጢአት ስንወድቅም የድኅነትን መንገድ አዘጋጅቶልናል።ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣ ይመሩን ዘንድ ነቢያትን ወደ እኛ ልኮልናል፤ኀሊና ቸሮናል፤ከዚህ በተጨማሪ አርቀን እናስተውል ዘንድ የሚያስረዳንን የተጻፈ ሕግ ሰጥቶናል።
- *ሥጋን* እንዲለብስ ግድ ያለውም የእኛ ፍቅር ነው።እርሱ ይህን የእኛ *ሥጋ* የለበሰው ሊቀድሰው ነው።እርሱ ስለ እኛ ሲል ሕግን በመቀበል ሰዎች እግዚአብሄርን የመፍራት መልክ እንዲኖራቸው አድርጎ በማቅረብ አባቱ እግዚብሔር አብን አስደስቷል።
- ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣም ስለ እኛ ሲል ***ሞቷል።"ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆነ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤.....***" 1ኛ ጴጥ 3፡18።
- እርሱ በመስቀል ላይ ሳለ ፍቅርን የሚያደል አምላክ ነበር።እርሱ የዓለሙን ኃጢአት በመሸከም በደሙ አጥቦል፣ እርሱ ምንም ኃጢአት ሳይኖርበት ስለ እኛ ኃጢአት ሲል እንደ ኃጢአተኛ ተቆጥሮአል። ይህን በማድረጉም በእኛ ፋንታ መላውን ካሣ ከፍሎአል።
- ስለ እርሱ ***"... በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከ መጨረሻ ወደዳቸው።"*** (ዮሐ 13፡1) ተብሎ ተጽፎአል።እንዲህም ተብሎ ተጽፎአል፦ ***"ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም።"*** ዮሐ 15፡13።
- ስለ ወደደንም እንዲህ ብሎናል። ***"ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤.... ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ።"*** ዮሐ 15፡15 ወንድሞቼ ብሎም ጠርቶናል፦ ***"...በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው።"*** ዕብ 2፡17። እኛም የሰማዩ አባት ልጆች ሆነናል፦ ***"የእግዚአብሄር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፤..."*** 1ኛ ዮሐ 3፡1።
- ፍቅሩን ሊያሳየን ስለ ፈለገም እንዲህ ብሎናል፦ ***"እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።"*** ማቴ 28፡20። ***"ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆለናሁ።"*** ማቴ 18፡20።
- ፍቅሩ በጥበቃው፤በእንክብካቤውና በማንኛውም ነገር ለእኛ በሚያደርገው አመራር ውስጥ ታይቶአል።

**ይቆየን።**